ጃንዋሪ 22, 2010

ለውድ ወላጆችና አሳዳጊዎች:

ይህን ደብዳቤ የጻፍኩት የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችንና መምህራንን የዘርና የብሔር አመጣጥ በሚመለከት የመረጃ አሰባሰብ በተያያዘ በዩኤስ የትምህርት ክፍል የመጣውን አዲሱን የአሠራር መመሪያ ለማሳወቅ ነው። ሁሉም ስቴቶች ይህን መረጃ እንዲያሰባስቡ የሚጠይቀው የፌዴራሉ መንግስት አዳዲስ ምድቦችን የሚያጠቃልል የብሔር አመጣጥና የዘር ሪፖርት አቀራረብ አዲስ አሠራር አውጥቷል።

የፌዴራሉ መንግስት እነዚህን አዳዲስ ምድቦች ያዘጋጀው የአገሪቱን የብሔርና የዘር አመጣጥ ስብጥር የሚያሳይ የተሻለ ትክክለኛ ገጽታ ለማስገኘት ነው። ይህ ግለሰቦች እንዳስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ በሆኑ የዘር ምድቦች በብሔርና በዘር ክፍፍል እንዲለዩ ለማድረግ የሚያስችል ይሆናል። ቀደም ሲል የነበረው የአሠራር መመሪያ ግለሰቦች በአንድ የዘር ምድብ ብቻ እንዲለዩ የሚፈቅድ ነበር።

የተማሪዎች መረጃ በአዲሱ የብሔርና የዘር ምድብ መሠረት መረጃው በአሁኑ ጊዜ በሚሠራበት በአንድ አይነት መንገድ ይሠራበታል። ለምሣሌ የፌዴራል መንግሥትና የኮሎራዶ ስቴት እንደ ኮሎራዶ ስቴት ግምገማ ፕሮግራም (ሲኤስኤፒ) ነጥብ አጠቃላይ የፈተና ውጤት እና እንደ ተመራቂ ተማሪዎች ወይም ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎች መጠን በመሳሰሉ አጠቃላይ የማሪዎች የውጤት መረጃዎች ሪፖርት አቀራረብና ትንተና የዘርና የብሔር መረጃ ይጠቀማሉ። እነዚህ ሪፖርቶች በተማሪዎች የትምህርት ተሳትፎ፣ እንቅስቃሴና ውጤት ውስጥ በየጊዜው የሚታዩትን ለውጦች በመከታተል ሁሉም ተማሪዎች የሚገባቸውን የትምህርት ፕሮግራምና አገልግሎት ማግኘታቸውን ለማረጋገጥ ይረዱናል።

ከዚህ ተያይዞ የቀረበውን መጠይቅ በመሙላት በራስ በተፃፈ አድራሻ እስከ ማርች1/ 2010 መልሰው ይላኩልን። ለአሠራር እንዲያመችዎ በአሁኑ ወቅት በመዝገብ የተያዘው የልጅዎ የዘር/የብሔረሰብ መረጃ ቀርቦልዎታል። ይህን መረጃ መስጠት ካልፈለጉ ለዚህ መጠይቅ በእርስዎ ስም ኤፒኤስ መልስ መስጠት እንዳለበት አስታውሱ። የፌዴራሉ መንግሥት ከየስቴቱና በየዲስትሪክቱ አጠቃላይ አሐዝ በማግኘት ረገድ መረጃው ሳይሰበሰብ ከሚቀር በዚህ መንገድ የተሟላ መረጃ ማግኘት ተራጭነት እንደሚኖረው ያምንበታል።

የተማሪ መረጃንና የሪፖርት አቀራረብ ምድቦችን በሚመለከት ለተጨማሪ መረጃ ሊህ ዊልኪንሰንን በስልክ ቁጥር 303-344-2209 ማነጋገር ይቻላል።

የልጅዎን ትምህርትና በኮሎራዶ አክሪዲቴሽን ደምብ መሠረት የኤፒኤስ ውጤቱን እንዲሁም *ኖ ቻይልድ ሌፍት ቢሃይንድ አክትን* በሚመለከት እንዴት ማወቅ እንደሚችሉም መረጃ ልናካፍልዎት እንፈልጋለን። የሲኤስአፒ ውጤትን፣ በቂ አመታዊ ለውጥን፣ የመምህራንን ብቃት፣ የተመራቂዎችንና ትምህርት ያቋረጡ ተማሪዎችን መጠን፣ እንዲሁም የኤሲቲ ነጥብን በሚመለከት ለተጨማሪ መረጃ በድረ ገጽ አድራሻ www.aps.k12.co.us/update/ ይመልከቱ። የዚህን መረጃ ቅጂ ማግኘት ከፈለጉ በስልክ ቁጥር 303-365-7805 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ።

ከልብ፡

ጆን ሊ. ባሪ
የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንቴንዳንት

አባሪ: ለወላጆች/ለአሳዳጊዎች የተዘጋጀ መጠይቅ